ቀን ፣ታህሳስ 27/2000ዓ.ም

# የቅንጅት የድጋፍና የዕድገት ድርጅት በኖርዌይ
# የአቋም መግለጫ

ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ባለው የጠራ ራዕይ በአጭር ጊዜ ባሳየው የመወዳደር ብቃትና ባገኘው ሕዝባዊ አመኔታ ሽብር የገባው የገዢው ቡድን ንፁህን ኢትዮጲያውያንን በመረሸን፣በማሰርና ለስደት ከመዳረግ ባሻገር ቅንጅትን ለማጥፋት ያልፈነቀለው ድንጋይ ወይም ያልተጠቀመው መንገድ የለም።

ቅንጅት ከወያኔ የሚሰነዘርበትን የማዳከምና የማጥፋት ሴራ እየተቋቋመ ቢገኝም በአመራር አካላቱ መሀከል የተፈጠረው ችግር ከማንምና ከምንም በላይ ቅንጅትን ከማዳከሙም ባሻገር ደጋፊዎቹንም አንገት እያስደፋ ይገኛል።ይህ ሁኔታ ጉዳዩ የማይመለከታቸው ሃይላትን ሁኔታው በፈጠረላቸው ቀዳዳ በመጠቀም የድርጅቱን ውስጣዊ ችግር ለማባባስና ለማዛባት ዕድል ስለሰጣቸው ቅንጅትን በማዳከም ተልዕኮአቸው እንዲገፉበት አስችሎአቸዋል፡፡

እኛ በኖርዌይ የምንገኝ የቅንጅት የድጋፍና የዕድገት ድርጅት አባላት ቅንጅትን የምንደግፈው በዲሞክራሲያዊ መርሀ-ግብሩ፣ ከቅንጅት ራዕይ አንፃር በመነሳት፣ በህግና ደንብ የበላይነት የሚመራ ፓርቲ መሆኑን በማመን ነው። ይሁንና በአመራር አካላቱ የተፈጠረው አለመግባባት ከቅንጅት መርህ አኳያ የግለሰብ ሚና የማይናቅ መሆኑን ብናምንም አምባገነናዊ ዝንባሌን ማሳየት ኢትዮጲያን ከድጡ ወደ ማጡ ማስገባት መስሎ ይሰማናል።
ከዚህ በኩረ-ሀሳብ በመነሳት፥

1. በቅንጅት ፓርቲ ሊቀመንበር በኢንጂነር ሃይሉ ሻውል አምስት ከፍተኛ የአመራር አባላትን ከፓርቲው ማገዳቸውና ያገዱበትን ምክንያት በጥሞና ተከታትለናል። ይህ ሊቀመንበሩ የወሰዱት እርምጃ ከቅንጅት መርህና ራዕይ ፍፅም የሚቃረንና እኛም ልንቀበለውና ልንደግፈው የማንችለው በመሆኑ ይህን ግለሰባዊ ውሳኔያቸውን በአስቸኳይ እንዲያነሱ ጥሪ እናደርጋለን።

2. በፓርቲያችን የአሠራር ደንብ መሠረት ሊቀመንበሩ ከሌሉ ወይም መሥራት ካልቻሉ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበርና

ከዚያም በተዋረድ ያሉት የሥልጣን አካላት ተክተው መስራት እንደሚገባቸው እየታወቀ ከህግና ደንብ ውጪ አቶ አባይነህ ብርሃኑን መወከላቸው እጅግ አሳዝኖናል።በመሆኑም የሰጡትን ውክልና በመሰረዝ በፓርቲው ደንብ መሠረት እንዲሰራ አጥብቀን እንጠይቃለን።

3. ከዚህም በላይ ፓርቲያችን ከገባበት የውስጥ ችግርና ቀውስ ለመላቀቅ በመግባባትና በውይይት ሕዝባዊውን ትግል ከግቡ ማድረስ ይችል ዘንድ ሁሉም የአመራር አባላት ታሪካዊና ሕዝባዊ ግዴታቸውን እነዲወጡ እንጠይቃለን።

4. የቅንጅትን መርህና ራዕይ ያልተከተለ አሰራር ማንኛውም አካል እንደማያራምድ ያለንን እምነት እየገለፅን ከዚህ ውጪ ከትግሉ መስመር የሚያስወጣ ማንኛውም እንቅስቃሴን የማንደግፍ መሆናችንን እያስተወቅን ቅንጅትን እስከዛሬ እንደደገፍንና እንደተሳተፍን ሁሉ ለወደፊቱም ትግላችንን አጎልብተንና አጠናክረን ለቅንጅት ራዕይ እውን መሆን በቁርጠኝነት መቆማችንን እናረጋግጣለን።

ድል ለኢትዮጲያ ሕዝብ!!!!!

የቅንጅት የድጋፍና የዕድገት ድርጅት በኖርዌይ